# የጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አሕመድ የመደመር የለውጥ ሂደት እና የህዝብ አስተያየት

# የፌስቡክ ጥናት ውጤት

(በሓምሌ 24፣ 2010 ዓ.ም. - ነሓሴ 15፣ 2010 ዓ.ም.)




## 1. መግብያ

ካለፈው መጋቢት ወር መጨረሻ ጀምሮ ኢትዮጵያ አዲስ ጠቅላይ ሚኒስተር በመምረጥ "መደመር" በሚል ስያሜ የለውጥ ጉዞ ትገኛለች፡፡ በዚህ መደመር ሂደት በርካታ አዎንታዊና አሉታዊ ክስተቶች ተከስቷል፡፡ በማህበራዊ ሚድያ የተለያዩ አመለካከቶች ሲንፀባረቁ ይታያል፡፡ ማህበራዊ ሚድያ ባለፉት 4



ከህዳሴ ኢትዮጵያ hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com

ወራት ታይቶ በማይታወቀው መልክ በፎቶግራፎች፣ ገንቢ እና አፍራሽ ሃሳቦች፣ ሙገሳዎችና ስድቦች፣ ወዘተረፈ ትእይንቶች ተስተውሏል፡፡

ከዚህ በመነሳት በአገራች እየተካሄደ ያለው የለውጥ ሂዴት ህብረተሰቡ በተለይ የሶሻል ሚድያ ተጠቃሚ እንዴት ያየዋል፣ በለውጡ ደስተኛነው ወይስ አይደለም፣ የጠ/ሚንስተራችን አካሄድስ እንዴት ነው ለቦታው ይመጥናሉ ብሎ ያምናል ወይስ አያምንም የሚሉ ሁኔታዎችን በማወቅ ከዚህ የሚገኝ ውጤት መሰረት በማድረግ መስተካከል የሚገባቸው ነገሮች ካሉ በማስተካከል ለውጡ ለአገራችን ህዳሴ በሚበጅና ለሁሉም ህዝቦች በሚጠቅም መንገድ እንዲወሰድ ከሚል ዓላማ በመነሳት ነው ይህ ጥናት የተካሄደው፡፡

## 2. የፌስቡክ አስተማማኝነትና የጥናቱ ሂደት

ሁሉም እንደሚያውቀው በተግባርም እያየነው ያለው ነገር በተለይ *ባለፉት ሁለት እና ሶስት ዓመታት በአገራችን ያልተደረገ ነገር፣ በሌሎች የአርፍሪካና የኤሽያ አገሮች የተከሰተ አፀያፊ ፎቶግራፎችን በመለጠፍ፣ ያልተቃጠለ እንደተቃጠለ በማስመሰል፣ ያልሞተ ሞተ በማለት ወይም የሞተ አጋንኖ በማቅረብ የተሳሳተ መረጃ ሲሰጥ ይስተዋላል፡፡ስለዚህ እንዲህ አይነት መረጃ ያለበት ፌስቡክ እንዴት የጥናት ምንጭ ሊሆን ይችላል?* የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም፡፡ መቅረቡ ትክክልም ነው፡፡

ለዚህ ዓላማ በተቻለ መጠን ፌስቡክ እንዴት ሓቀኛ መረጃ ማግኘት እንችላለን የሚል በማሰብ ለያንዳንዱ የፌስቡክ ተጠቃሚ *የራሱን አስተያየት ብቻ እንዲሰጥ የሚያስችል ስልት በመጠቀም ነው* ይህን ጥናት ለማካሄድ የሞከርነው፡፡ *ስለዚ የተጋነነ፣ ያልሆነ በሬ ወለደ፣ ያልተፈጠረ ተፈጠረ ተባለ የሚባሉ የፌስቡክ ስሞታዎች እዚህ ጥናት ላይ ቦታ የላቸውም፡፡* ምክንያቱ እዚህ *የተጠቀምነው መረጃ እያንዳንዱ ድምፅ ሰጪ የራሱ ስሜት ብቻ የሚገልፅ ብቻ በመሆኑ፡፡* ዋናው ነገር የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ አንድን ሰው

አንድ ድምፅ ብቻ ያለው ሲሆን ሁለተኛና ሶስተኛ ድምፅ በአንድ አካውንት የሚሰጥበት እድል የለም፡፡

## *3. የጥናቱ ሽፋን እና አስፈላጊነት*

ስለዚ ከዚህ በታች ያሉ የድምፅ ሰጪዎች ቁጥር የሚያመለክቱ የየራሳቸው ኣስተያየት ብቻ እንዲሰጡ የተደረጉ ናቸው፡፡ ስለዚ ለዚህ ጥናት ፌስቡክ አሉታዊ ጎኑን ሳልጠቀምበት አዎንታዊ ጎኑን ብቻ በመውሰድ አስተማማኝ እንዲሆን ለማድረግ ተሞክረዋል፡፡ ማንም ሰው የፌስቡክ ፔጁ ላይ ገብቶም ድምፅ እንዲሰጥ፣ ውጤት እንዲያይ ክፍት ነው፡፡ ***ስለዚ የድምፁ ቆጠራ በማህበራዊ ሚድያ እንደሚታየው የተጋነነ ቁጥሮች የሚደረደርበት ወይም ያልተፈለጉ ቁጥሮች የሚቀነሱበት ሁኔታ የለም ቢፈለግም አይቻልም፡፡*** ስለዚህ ይህ የጥናት ውጤት ኣስተማማኝ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ማንም ሰው ፔጁ ገብቶ ማረጋገጥም ይችላል፡፡

***በጥናቱ የተሳተፉ አንዳንድ ሰዎች አስተያየት ሲሰጡ፣ ራሳቸው ድምፅ ከሰጡና ውጤቱን ካዩ በኋላ የትግራይ ተወላጆች እና የህወሓት አባላት ብቻ ናቸው የሰጡ ስለዚ ዋጋ የለውም በማለት አስተያየት የሰጡ አሉ፡፡*** ነገር ግን ሓቁ እንደዛ አይደለም፡፡ እነሱ ራሳቸው ማንም ሳይከለክላቸው ድምፅ እየሰጡ እንዲህ ማለታቸው፣ የአብዛኸኛው ድምፅ ውጤት ያለመቀበል መሆኑ ያሳያል፡፡ ማንኛውም ሰው በፔጁ ላይ ሄዶ ማረጋገጥ ይችላል፡፡ እንደ ፌስቡክ ተጠቃሚ አከባቢ የምትመርጥበት ዕድሉ ቢኖርም በኛ በኢትዮጵያውያን ግን ይህን ለይቶ ተጠቃሚ የማድረግ ብዙ የተለመደ አይደለም *(የህዳሴ ኢትዮጵያ ፔጅም አከባቢ ሳይመርጥ ለሁሉም ክፍት ነው)* ፡፡ ***ስለዚ በኔ እምነት ይህ ጥናት የአንድ ክልል ብቻ አይደለም፣ ሁሉም የአገራችን ክፍሎች ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያውያን ዳያስፖራም ጭምር ያካተተ ነው፡፡***



*ከህዳሴ ኢትዮጵያ hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com*

ይህ በእንዲህ እያለ የአንድ አከባቢ ቢሆንስ? ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የለውጥ ሂደት አንድ ክልል የሚያክል ህዝብ ካልደገፈው ለውጡ በምንም ተአምር ኢትዮጵያን ወደተሻለ ለውጥ የሚወስድ አይሆንም፡፡ የተከበሩ ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ እንዳሉት አንድ መኪና መኪና ሆኖ ሊያገለግል የሚችለው የተለያዩ የመኪናዋ ክፍሎች ተቀናጅተውና ተወሃህደው ሲሰሩ ነው፤ *ስለዚ የመኪናው አንዱ ክፍል ካልተቀናጀ ወይም ካልተወሃሃደ መኪናው ሊጓዝ አይችልም፡፡ ስለዚ አንድን ሾፌር ጉዞ ከመጀመሩ በፊት ሁሉንም ክፍሎች በትክክል እየሰሩ መሆናቸው፣ እየተቀናጁና እየተወሃሃዱ መሆናቸው የማረጋገጥ ከፍተኛ ሃላፊነት ኣለበት፡፡* አለበለዚያ መኪናው አይሰራም ሹፌሩም ሹፌር አይባልም፡፡ ***ስለዚህ ይህ ጥናት ማጣጣል ሳይሆን የሚያስፈልገው የአንድ ክፍል ይሁን የሁሉም ክፍል አስተያየቶቹን ወስዶ ለውጡ የሁሉም ማድረግ ይገባል፡፡ አንዱን ክፍል ትቶ መጓዝ ለውጡ ሙሉ አያደርገውም፡፡ ስለዚ ጠቅላይ ሚኒስተር ዶ/ር አብይ አሕመድ ምንም ወጪ ሳያወጡበት፣ ምንም ድካም ሳይደክሙበት፣ ለአገር አንድነት፣ ሰላም እና መረጋጋት እንዲሁም ለአገር ልማትና የተጀመረው የህዳሴ ጉዞ ቀጣይነት ከሚጨነቁ ዜጎች የተበረከተላቸው ስጦታ (ይህ ጥናት) ተቀብለው ቢጠቀሙበት ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ይጠቅማል፡፡***

*ይህ ከተጠቀምንበት የለውጡ ሂደት ለህዝብና ለአገር ጥቅም ማዋል እንችላለን፡፡ ካልተጠቀምንበት ደግሞ ፍፃሜዎች እና ሁኔታዎች ወደ መሩን እንሂዳለን፡፡ የአንድ አመራር ብልህነት የሚመዘነው በየጊዜው የህዝቡን ልብ ትርታ በማድመጥ ችግሮቹን እና ጥንካሬዎቹን ለይቶ ጥንካሬዎቹ በበለጠ ማጎልበት ችግሮቹ ደግሞ ስር ሳይሰዱ እየተከታተለ እግር በእግር እንዲፈቱ በማድረግ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በለውጡ ዙርያ ማሰለፍ ከቻለ ነው፡፡* **ስለዚህ የኢህአዴግ ሊቀመንበር ዶ/ር አብይ አሕመ ከጭፍን ደጋፊዎቻቸው እየወረደ ያለው ሙገሳና አድናቆት ወደ ጎን ትተው** የኢትዮጵያ ህዝብ ከጫፍ

ጫፍ፣ ሁሉንም ብሄር-ብሄረሰብ፣ ሁሉንም እምነት፣ ሁሉንም ያታ፣ አርሶአደሩም ከተሜውም፣ ያገርውስጥም የውጭ ዳያስፖራም ምን ይላል? ለውጡ እንዴት ያየዋል? በለውጡ ሂደት እና ውጤት ተጠቃሚ ማነው? ተጎጂስ ይኖራል ወይ? ካለ ማነው? ለምን ሆነ? እንዴትስ ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል? የሚሉ ጥያቄዎች በመጠየቅ መስራት ከጀመሩ ያለምንም ጥርጥር የህዳሴ ጉዞው ማስቀጠል ይቻላል፣ ካልሆነ ግን የህዳሴ ጉዞው በመቀልበስ ወደ ፋሽዝም መለወጡ አይቀሬ ነው፡፡ይህ ደግሞ ለማንም የማይጠቅም የዜሮ ድምር የቁማር ጨዋታ ነው፡፡

ስለዚ የተከበሩ ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አሕመድ የአገራችን ህዝቦች አስተያየቶችና ጥያቄዎች እየተከታተሉ መስተካከል የሚገባቸው ነገሮች ያስተካክላሉ የሚል ታሳቢ በማድረግ ነው ይህ ጥናት እያቀረብኩ ያለሁት፡፡ ስለዚ ጠቅላይ ሚኒስተራችን እድለኛ ናቸው ምንም ወጪ ሳያስወጡ የዚህ ጥናት ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ የዚህ ጥናት ውጤት ቸል ማለት የለበትም የሚል እምነት አለኝ፡፡ የዚህ ጥናትና ውጤት አቅራቢው "ህዳሴ ኢትዮጵያ" አገራችን ኢትዮጵያ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ወይም ልማታዊ ዴሞክራሲ መስመር በመከተል የጀመረችውን የህዳሴ ጉዞ በተሳካ መንገድ እንዲቀጥል እና የጀመረችውን ሕገ-መንግስታዊና ፌደራላዊ ስርዓት በማጠናከር ሳይሸራረፍ ለማስቀጠል የሚጥር በመሆኑ፤ ለአገራችን አንድነት፣ መቻቻል፣ መከባበር፣ ሰላም፣ መረጋጋትና ልማት የሚጠቅሙ ነገሮችን የሚያበረታታና፣ አፍራፍ እንቅስቃሴዎችን የሚቃወምና የሚታገል የፌስቡክ ፔጅ በመሆኑ እንደዚህ አይነቶች ጥናቶችና ትንታኔዎች እየተከታተለ ያቀርባል፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢ ፍላጎት ወይም ዓላማ በዚህ ጥናት መሰረት ማስተካከያዎችን በመውሰድ ለውጡ የሁሉም ብሄርብሄረሰቦችና ህዝቦች ሆኖ የተጀመረውን የህዳሴ ጉዞ በተሳለጠ አኳሀን እንዲቀጥል ነው፡፡

## 4. የጥናቱ ውጤት

የጥናቱ ሁኔታ ይህ ካልኩ ምንድ ነው ውጤቱና ትንታኔው የሚለው ከዚህ ቀጥየ አቀርበዋሎህ፡፡ የጥናቱ ውጤት በሁለት በመክፈል ለማቅረብ እፈልጋለሁ፡፡ አንደኛው ክፍል አሃዛዊ Quantitative መረጃው እንደወረደ በፐርሰንት በማሰላት ሳቀርበው ሌላኛው ደግሞ የግል አስተያየቶች ትዝብቶች Subjective or Qualitative ክፍሉ ደግመ ከተጨባጭ ሁኔታዎችን በማገናዘብ ሁለቱም ክፍሎች በማናበብ ለማቅረብ ተሞክረዋል፡፡ ኣሃዛዊ ውጤትም በሁለት ክፍሎች በመክፈል እናየዋለን፡፡ አንደኛው ክፍል ሶስት ሳምንት ያደረገው ጥያቄ ማለትም "መደመር እንዴት ታየዋለህ?" በሚለው ያተኮረ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ "ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አሕመድ በስልጣን ይቀጥሉ ወይስ ይውረዱ?" በሚለው ጥያቄ በማትኮር ይሆናል፡፡

### 4.1 "መደመር እንዴት ታየዋለህ?"

የመጀመሪያው ጥያቄ በፌስቡክ ከተለቀቀ ሶስት ሳምንታት ያደረገ በመሆኑ፣ በነዚህ ሳምንታት የተሳታፊው ድምፅ ምን ይመስላል የድምፁ ሰጪዎች አስተያየት አቅጣጫ ወይም (Trend) ምን ይመስላል የሚለውን በደንብ ለመረዳት በየሳምንቱ ከፋፍየ አቀርበዋለሁ፡፡

#### 4.1.1 በመጀመሪያው ሳምንት

መደመር እንዴት ታየዋለህ የሚል ጥያቄ በፌስቡክ ገፆች የቀረበው ከሶስት ሳምንት በፊት በሓምሌ 24፣ 2010 ዓ.ም. ሲሆን በየሳምንቱ የነበረው የተሳትፎ ብዛት ሲታይ በመጀመሪያው ሳምንት ጥናቱ ወደ 8384 ሰዎች የደረሰ ሲሆን፣ ከነዚህ ውስጥ 604 ሰዎች ወይም 7.2% ብቻ ነበር መልስ የሰጡት፡፡ ***ከነዚህ 604 ሰዎች*** ለመደመር እንዴት ታየዋለህ የሚል ጥያቄ መልስ የሱት ውስጥ ኣብዛኛዎቹ ማለትም ***386 ሰዎች ወይም 63.9%*** መደመር የሚባለው ፈሊጥ

*ትክክል እንዳልሆነና እንደማይቀበሉት* ሲገልፁ የተቀሩት *218 ሰዎች ወይም 36%* ግን መደመር የሚባለው *ለውጥ ወቅታዊና ትክክል እንደሆነ፣ እንደሚደግፉት ገልፆዋል፡፡ይህን ጥናት በተጀመረበት ጊዜ በመጀመሪያዎቹ ሁለት እና ሶስት ቀናት መደመር የሚደግፈውን ሰው በብዛት ድምፅ ሲሰጥ የነበረ ሲሆን ከፍተኛ ፉክክር የታየበት ነበር፡፡ሆኖም ግን በስተመጨረሻ መደመርን የሚቃወም ሰው በመብዛቱ ውጤቱ እንደተገለፀው ሆኖዋል፡፡*

### 4.1.2 *በሁለተኛው ሳምንት*

በሁለተኛው ሳምንት የድምፅ አሰጣጡ ሁኔታ ሲታይ ቀዝቀዝ ብሎ የነበረ ሲሆን ወደ 445 ሰዎች ብቻ በመድረሱ ከነዚህ ውስጥ ግን 78 ሰዎች ወይም 17.5% ድምፅ ሰጥቷል፡፡ ምንም እንኳ የተደራሽነቱ ካለፈው ሳምንት ሲነፃፀር አነስተኛ ቢሆንም የድምፅ ሰጪዎች ሁኔታ ሲታይ ግን በአመዛኙ ማለትም ከ74 ድምፅ ሰጪዎች 13 ሰዎች ወይም 17% ብቻ መደመርን የሚደግፉ ሲሆኑ ኣብዛኞቹ ማለትም 65 ሰዎች ወይም 83% የመደመር ሁኔታ ያንገሸገሻቸው እንደሆነ እና እንደማይደግፉት የገለፁ ነበሩ፡፡

አጠቃላይ የሁለተኛው ሳምንት ጥናት እንደሚያሳየው ከሆነ የመደመር እና የጠ/ሚ ዶ/ር አብይ በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ *የነበራቸው ድጋፍ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ እና ከሰኔ 16፣ 2010 ዓ.ም. ተደምረው የነበሩ የህብረተሰብ ክፍሎች እየተቀነሱ መምጣታቸው እንደሆነ* ባለፉት ሁለት ሳምንታት የተሰጠው የህዝብ አስተያየት ያሳያል፡፡ *ለዚህም ምክንያት ይሆናል ተብሎ የሚገመተው በሶማሌ ክልል የነበረው የሰላም እጦት፣ በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች እየታዩ ያሉ ያለመረጋጋትና በየቀኑ እርስበርሳቸው የሚጣረሱ መግለጫዎች፣ ትዕይንቶች፣ ወዘተ ህዝቡ መደመርን እንዲጠላና እንዳይደግፈው አድርጎታል የሚል እምነት ነበር፡፡*

ይህ ሁኔታ ተደማምሮ አጠቃላይ የሁለት ሳምንቱ ውጤቱን የደረሰበት ሁኔታ ሲታይ የጥናቱ መሪ ጥያቄ ወደ 8829 ሰዎች የደረሰ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 682 ሰዎች ወይም 7.7% ብቻ ድምፅ ሰጥቷል፡፡ ከነዚህ ድምፅ የሰጡት 682 ሰዎች ውስጥ ኣብዛኛዎቹ ማለትም ***451 ሰዎች ወይም 66% የመደመር ሂደቱና ውጤቱን የሚቃወሙ*** ሲሆን የተቀሩት ***231 ሰዎች ወይም 34% ግን መደመር እንደሚደግፉና በመደመር ምክንያት እየታየ ያለው ያለመረጋጋት ጊዚያዊና የለውጥ ባህሪ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡***




መረጃዎች ተሰብስበው የሁለት ሳምንት የጥናት ውጤት ትንታኔ በሚሰራበት ወቅት አንድ ***አስነዋሪና በአገራችን ታይቶ የማይታወቅ የአረመኔዎች ተግባር በሻሸመኔ ከተማ በመፈፀሙ መላው የአገራችን ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦችን ያስደነገጠ እና ወደ ትልቅ ስጋት ያስገባ ነበር፡፡*** በዚህም ጊዜ የጥናቱ ሪፖርት ይህን በሻሸመኔ የተፈፀመው አስነዋሪ ተግባር፤ ***የመደመር እና የለውጥ ሂደቱ በኢትዮጵያ ህዝቦች ዘንድ የነበረውን ተቀባይነት ክፉኛ እንደሚጎዳው እና***

***ወደ አልተፈለገ መንገድ ሊያመራ ስለሚችል የተከበሩ ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አሕመድ በሰከነና በተረጋጋ መንፈ የለውጡ ሂደት ገምግመው እንዲመሩት ሪፖርቱ በሚከተለው አገላለፅ አመላክቶ ነበር፡፡***

> ***ትናንት በሻሸመኔ የተፈፀመው አስነዋሪ ድርጊት ደግሞ ህዝቡ በበለጠ የመደመር ሂደቱ እንዲጠላ የሚያደርግ እንደሆነ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ስለዚ አሁንም ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ ጊዜ ሳይሰጡ የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ሰብስቦ የለውጡ ሂደት በሰከነ መንፈስ በመገምገም ለውጡን የህዝብ ፍላጎት በሚያሟላ መልኩ እንዲመሩት ይጠበቃል፡፡ አለበለዚያ አደጋው በጣም ከፍተኛ ነው፡፡***

የሚል ነበር፡፡

## *4.1.3 በሶስተኛው ሳምንት*

የሶስተኛው ሳምንት የጥናቱ መረጃዎች እንደሚያሳዩት የድምፅ አሰጣጡ ሁኔታ ከሁለተኛው ሳምንት በበለጠ የተጧጧፈበት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ***ምክንያቱ በሁለተኛው ሳምንት የጥያቄው ተደራሽነት ለ445 ሰዎች ብቻ የነበረ ሲሆን የሶስተኛው ሳምንት ግን ለ3135 ነበር፡፡ ይህም ከ7 እጥፍ በላይ ያደገ ሲሆን፤*** ከዚህ ተደራሽነት ድምፅ የሰጡ ደግሞ 351 ሰዎች ሲሆኑ ***ከሁለተኛው ሳምንት ድምፅ የሰጡ 78 ሰዎች ሲነፃፀር ከ4 እጥፍ በላይ ሆኖዋል፡፡ ለምን በሶስተኛ ሳምንት በተጋጋለ ሁኔታ ድምፅ ለመስጠት ተነሳሳ የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡በዋናነት በአገራችን እየተስተዋለ ያለውን ብጥብጥ፣ በአሰቃቂ ሁኔታ ሰው መግደል፣ ንብረት ማውደም፣ የዜጎች ሰብአዊ መብቶች መገደብ፣ ያለ ክልሎች ፈቃድ ታጣቂዎች ማሰማራት ሁኔታዎችና በአጠቃላይ አሁን በአገራችን ነግሶ ያለውን ስርዓት አልበኝነት ሁኔታ ስላማረረው የፈጠረው ስሜት ነው በተጋጋለ ሁኔታ ፍላጎቱን በፌስቡክ መግለፁን የቻለው፡፡ከዚህ በተጨማሪም የሁለተኛው ሳምንት ሪፖርት መቅረቡም የብዙ ሰዎች ስሜትን በመቀስቀሱ የጥናቱን ተሳታፊ መሆን***

***በመምረጡም አንድ ምክንያት ነው፡፡*** በዚህ ሶስተኛው ሳምንት ብቻ የተገኘው መረጃ ወስደን ብናይ ጥያቄው ከደረሳቸው 3135 ሰዎች ውስጥ 351 ሰዎች ***ወይም 11.2% ብቻ ድምፅ የሰጡ*** ሲሆን ከባለፊው ሳምንት የ5% ቅናሽ አለው፡፡ ማለትም ድምፅ ሰጪዎች እንደ ተደራሽነቱ አይደለም ነገር ግን ከአጠቃላይ ***ካሁን በፊት የተደረጉ ጥናቶች ሲነፃፀር በእጥፍ ያደገ ነው፡፡***

የነዚህ 351 ድምፅ የሰጡ ሰዎች ውጤት ስናይ አሁንም ኣብዛኛው ሰው ማለትም 279 ሰው ወይም *79.5% የመደመር ሂደቱም ውጤቱም አምርረው የሚቃወሙ ሲሆኑ የተቀሩት 72 ሰዎች ወይም 20.5% ደግሞ በመደመር ሂደቱም ውጤቱም እርካታ ያገኙና የሚደግፉት እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡*

***አጠቃላይ የሶስተኛው ሳምንት ጥናት*** እንደሚያሳየው፣ በመደመር ስም የሚጠራው ***የለውጥ ሂደት ከጊዜ ወደ ጊዜ ተደማሪዎች እያንጠባጠመ የህዝቡ ድጋፍ እያጣና መሆኑ ያሳያል፡፡*** የጥናቱ መረጃ እንደሚያሳየው በመጀመሪያው ሳምንት የለውጡ ደጋፊዎች *36%* የነበረ ሲሆን በ2ኛ እና በ3ኛ ሳምንት ደግሞ *34%* እና *29%* ሆኖዋል ይህም ትርጉሙ ***በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ የነበረው ድጋፍ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ በአንፃሩ ተደምረው የነበሩ የህብረተሰብ ክፍሎች እየተቀነሱ ወደ ተቃዋሚው ጎራ መሰለፋቸው ባለፉት ሶስት ሳምንታት የተሰጠው የህዝብ አስተያየት ያሳያል፡፡***በተለይ በሶስተኛ ሳምንት የመቀነሱ ሁኔታ ሲታይ *ከሁለተኛ ሳምንት (2%) ከእጥፍ በላይ (5%) መቀነሱ* የህዝቡ ቅሬታ ከጊዜ ወደ ጊዜ ገከፍተኛ ፍጥነት እያሽቆለቆለ መሆኑ የሚያሳይ ምልክት ነው፡፡

ይህ ሁኔታ ተደማምሮ አጠቃላይ የሶስት ሳምንቱ ውጤቱን የደረሰበት ሁኔታ ሲታይ የጥናቱ መሪ ጥያቄ ወደ 11964 ሰዎች የደረሰ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 1033 ሰዎች ወይም 8.6% ብቻ ድምፅ ሰጥቷል፡፡ ከነዚህ ድምፅ የሰጡት 1033 ሰዎች ውስጥ ኣብዛኛዎቹ ማለትም *730 ሰዎች ወይም 71% የመደመር*

*ሂደቱና ውጤቱን የሚቃወሙ ሲሆን የተቀሩት 303 ሰዎች ወይም 29% ግን መደመር እንደሚደግፉና በመደመር ምክንያት እየታየ ያለው ያለመረጋጋት ጊዜያዊና የለውጥ ባህሪ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡*




## *4.2 "ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አሕመድ በስልጣን ይቀጥሉ ወይስ ይውረዱ?"*

የመጀመሪያው ጥያቄ ማለትም "መደመር እንዴት ታየዋለህ?" የሚለው ለሶስት ሳምንታት አየር ላይ ከቆየ በኋላ ውጤቱንና የአብዛኛውን አስተያየት ሰጪ ሃሳብ በመውሰድ ሁለተኛ ጥያቄ ማለትም *"በእርስዎ አስተያየት ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አሕመድ ስልጣን ተረክበው ኢትዮጵያን በመምራት ረገድ እስከ አሁን ድረስ ካስመዘገቡዋቸው ስኬቶች እና ውድቀቶች መሰረት በማድረግ*



ከህዳሴ ኢትዮጵያ hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com

በስልጣን ይቀጥሉ ወይስ?" የሚለው ተጨማሪ የጥናት አጀንዳ በማድረግ ወደ ፌስቡክ ተጠቃሚዎች ተዘርግቷል፡፡ ይህም ልክ እንደ የመጀመሪያው ጥያቄ የአንድ ወገን አመለካከት ብቻ እንዳይሆን ወደ ተለያዩ አመለካከት የሚንፀባረቅባቸው ፔጆች ሼር ተደርጓል፡፡

የዚህ ጥያቄ ዓላማ የጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አሕመድ የስልጣን ቆይታ ለመወሰን አይደለም፡፡ አንድን በህገመንግስት የተመረጠ ባለስልጣን በፌስቡክ ይሁን በሌላ ሚድያ በተደረገ ጥናት መሰረት ከስልጣን አወርዳለሁ ብሎ የሚጥር ካለ ሞኝ ነው፡፡ በህገመንግስታዊ ስርዓታችን ስልጣን የሚያዘው ሕገ-መንግስቱ ባስቀመጠው መንገድ /በዴሞክራሲያዊ ነፃ ምርጫ ብቻ/ ነው፡፡ የዚህ ጥያቄ አላማ በአገራችን እየተካሄደ ያለው የመደመር እና የለውጥ ሂደት በቀጥታ ከጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አሕመድ ወደ ስልጣን ጋር ይያያዛል፡፡ ስለሆነም **የመጀመሪያው ጥያቄ ከለውጡ ሂደት ጋር የተያያዘ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከለውጡ አመንጪ ጋር በማያያዝ የህዝቡን ፍላጎት እና እርካታ ለማወቅ ነው፡፡**

በዚህ መሰረት ይህ ጠ/ሚ በስልጣን ይቆዩ ወይስ ይውረዱ የሚል ጥያቄ ወደ ፌስቡክ ከተለቀቀ ሶስተ ቀን ብቻ ያደረገ ሲሆን፣ ባለፉት ሶስት ሳምንታት ከተደረገው ጥናት በጣም ፈጣንና በአጭር ጊዜ በርካታ ሰዎች መልስ የሰጡበት ነው፡፡ ይህ ጥያቄ ለ13916 ሰዎች የደረሰ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 1043 ሰዎች ወይም 7.5% ብቻ ድምፅ ሰጥቷል፡፡ ድምፅ ከሰጡት 1043 ሰዎች ውስጥ አሁንም ኣብዛኞቹ ማለትም ***781 ሰዎች ወይም 75% በጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አሕመድ አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ሲሆኑ ምርጫቸውም ጠ/ሚኒስትሩ ኢትዮጵያን ያክል ትልቅ አገር የመምራት ብቃት ስለሌላቸው ከስልጣን መውረድ አለባቸው ብለዋል፡፡የተቀሩት 262 ሰዎች ወይም 25% ደግሞ በጠ/ ሚንስትሩ አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ሆኖው ጠቅላይ***



ህዳሴ ኢትዮጵያ hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com

***ሚኒስትሩ ኢትዮጵያን ያክል ትልቅ አገር የመምራት ብቃት ስላላቸው በስልጣን መቆየት አለባቸው ብለዋል፡፡***




በአጠቃላይ ሲታይ በመጀመሪያው ጥያቄ ማለትም ***"መደመር እንዴት ታየዋለህ?"*** እንዲሁም በሁለተኛው ጥያቄ ***"ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አሕመድ በስልጣን ይቀጥሉ ወይስ ይውረዱ?"*** የተሰጡ ምላሾች ተመሳሳይ እና የሚናበቡ ናቸው፡፡ ***የቁጥር ልዩነት ካልሆነ በቀር ሁለቱም በተመሳሳይ ውሳኔ ላይ የወደቁ ናቸው***፡፡ ***የመጀመሪያው ጥያቄ ላይ ደጋፊና ተቃዋሚ 30% እና 70% በተከታታይ ሲሆን በሁለተኛው ጥያቄ ደጋፊና ተቃዋሚ 25% እና 75% በተከታታይ ናቸው፡፡*** ስለዚ በዚህ ሰዓት ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አሕመድ እና የመደመር የለውጥ ሂደታቸው ***በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ተቀባይነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ በፍጥነት እየቀነሰ በመምጣት 25% መድረሱ ያሳያል፡፡***

የኢትዮጵያ ህዝብ በመጀመሪያ አከባቢ ለውጡን ደግፎ በነቂስ እንዳልወጣ ለምን ታድያ አሁን እየቀነሰ እየቀነሰ እዚህ 25%ላይ ደረሰ?

የዚህ ጥያቄ መልስ በቀጣይ ክፍል ይቀርባል ተጠባበቁ

ከህዳሴ ኢትዮጵያ
ነሓሴ 22፤ 2010 ዓ.ም.

አስተያየትዎን በሚከተለው የኢሜል አድራሻ ማድረስ ይቻላል
hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com